# *ፈሪ በገዛ ጠቡ ገላጋይ ይሆናል!*

*ከኢህአፓ ደጋፊዎች*

*የኢትዮጵያን ታሪክ የሚከታተሉ ሰዎች ሀገሪቱ ለነፃነትና ለሀገራዊ አንድነት ከፍተኛ ዋጋ ሲከፍል የኖረ ህዝብ እንደነበራት ይመሰክራሉ። ይሁን እንጂ! የሀገሪቱ ውስጣዊ የአስተዳደር ችግር ተቀርፎ አያውቅም። አሁን አሁንማ ከፍተኛ መስዋዕትነት ሲከፈልበት የኖረው የሀገር አንድነት ጉዳይ በቀኝ ገዥዎች የረቀቀ ደባ በጦርነት ሳይሆን፤ በእርስበርስ ሽኩቻ እንዲያከትም የተሰላ መሆኑ ይስተዋላል። ቅኝ ገዥዎች በፊት ለፊት ያደረጉትን ወረራ ከአንዴም ሁለት ሶስቴ ድል ሊጎናፀፉበት ባለመቻላቸው፤ በትምህርትና በስልጣኔ ሰበብ የራሳቸውን አስተሳሰብ ሊያስፋፉ የሚችሉበት ፊደል ቆጠርኩ ባይ ዘመናዊ ባንዳ በመፍጠር ውስጣዊ የአስተሳሰብና የእምነት ወረራ እንዲካሄድ ማድረጋቸው ገሀድ እየወጣ ነው።*

*ከዚህ ቀደም በሀገር ጥያቄዎች ላይ የሰላ ሂስ ሲያካሂዱና አልፎም በደማቸው ሀገራቸውን አስከብረው የኖሩ አርበኞችና ልጆቻቸው ተንቀውና ተረስተው እንደቆዩ ሁሉ ዛሬም በምትካቸው የባንዳ ልጆች መድረኩን እየተውረገረጉበት ነው። የውጭ አጋሮቻቸውም ቁልፍ ቁልፍ ስፍራዎችን እንዲይዙ ካስደረጉ በሁዋላ የአፄ ሀይለስላሴ መንግስት ፈሩን ለቆ እንዲጓዝ በማድረግ በመጨረሻም ውጥረት ውስጥ እንዲገባና እንዲወድቅ ረድተዋል። ተኪውም አቅምና ችሎታ እንዳይኖረው ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል። ኢትዮጵያዊነትን አጉልቶ ስህተቶችን አርሞ በቀጣይነት አንድነቱንና እኩልነቱን አረጋግጦ ሊጓዝ የሚያስችለውን መንገድ ሁሉ አረካከሰው በማቅረብ ለዚህ ላለንበት ወቅት አብቅተውናል። የሀገሪቱን ምሁር አንድም ለነሱ ጥቅም እንዲሰራ አለያም በሀገሩ ጉዳይ አያገባኝም ብሎ ተቀማጭ እንዲሆን አድርገውታል። ይህ ሁሉ ነገር የተፈፀመው አሁንም እየተፈጸመ ያለው ኢትዮጵያውያን በጊዜው ነቅተን ሀገራችንንና አንድነታችንን ለመጠበቅ የሚያስችለን አቅም ባለመፍጠራችን ነው።*

*በኢህአፓ አመራር ስር ተሰባስበው የነበሩ የሀገሪቱ ልጆች ድርጅታቸው ይህንን ደባ በመቃወም አልፎም የህዝብ ጠላት ያሰለፋቸውን ጭፍሮቹን በመታገልና ህዝብን ለማዋዛት እንዳይችሉ ለማድረግ ሲረባረቡ፤ በተጓዳኝም ህዝብ ንቃተ ህሊናውን አዳብሮ ለዘላቂ ትግል እንዲነሳሳ ግንባር ቀደም መስዋዕትነት ለመክፈል ሲዘጋጁ፤ አንዳንዶች የፈሪ ገላጋይ ሆነው በገዛ ጠባቸው ለአስታራቂነት ሲጋበዙ ማየት ምንኛ አስገራሚ ነው። ኢህአፓን እንደድርጅት ሊያኮራው የሚገባና የህዝብ አጋርነቱ አይበገሬ መሆኑ ተደጋግሞ እንደታየው የስር ነቀል ለውጥ አብሳሪነቱ አማራጭ የሌለው እንደሆነ እየተስተዋለ ነው። ህዝብ በጊዚያዊና ዘለቄታ በማይኖረው ዓላማ ላይ ተሰልፎ በመታገል ጊዜውንና ሀይሉን  እንዳያባክን ኢህአፓ መክርዋል። በየጊዜው ለህዝብ ዲሞክራሲያዊ መብት ይጠቅማል ያለውን ሁሉ በመርህ ደረጃ በመያዝ ለማታገያ አበርክቶዋል። ከዚህም መሃል ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት ጥያቄ" አንዱ ነበር። አንደ ኢህአፓ እምነት ከሆነ ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት፤ ከተማሪው፤ ካስተማሪው፣ ከወታደሩ፤ ከሴቶች ማህበር፣ ከሰራተኛው ማህበርና ከገበሬው ስብስብ በህብረት ሆኖ በጊዜያዊነት የሚያገለግል መንግስት መፍጠራቸው፤ ካንድ ወገን ብቻ*

ከመጣ ከወታደሩ መንግስት የተሻለ መልክ ያለው፣ ዲሞክራሲያዊ ባህልን ሊያጎለብት የሚችል ነው። በጊዜው ልንገነዘብለት ባንችልም ከዛሬ ላይ ቆመን ትናንትን ስናማትር ይህ እምነት ሃቀኛ ለመሆኑ መሸፋፈን አይቻለንም። ይሁን እንጂ! አሁን ድረስ በኢትዮጵያውያን ዘንድ እየተገፋ ያለው የትግል ፎርም መንግስት ነኝ ባዩን በመለማመጥ ድልን መቀዳጀት ይቻላል የሚል ነው። ይህ ደግሞ ቀድሞ ኢህአፓ ያለው ተደማጭነት አግኝቶ ቢሆን ኖሮ፤ የ30ና ከዚያም በላይ አመታት መቁጠር ባላስፈለገ ነበር። በጥራቱም ቢሆን፤ የያን ጊዜው ህዝባዊ ማህበራት፤ በይዘታቸው ሰፊና የሚመለከታቸውን ክፍሎች ያቀፈ ለመሆኑ፤ የዛሬውን የግለሰቦች የፓርቲ አሰባሰብ ሁኔታ መመልከቱ በቂ ነው። ከዚያን ጊዜው የተማሪ፤ የአስተማሪና የሰራተኛ ማህበራት ወዘተ ስብስብ፤ የዛሬው የጥቂት ግለሰቦችና ምሁራን የፓርቲ አወቃቀር የተሻለ ህዝባዊ ይዘት አለው ለማለት አይቻልም። የያን ጊዜው በእምነትና በፍላጎት በመደራጀት ነበር፣ ያሁኑ አደረጃጀት ደግሞ በገንዘብና በጥቅም ሆኖዋል።

ሌላው የኢህአፓ የትግል መፈክር "ዲሞክራሲ ያለገደብ" የሚል ነበር። ይህ መፈክር አንዳንድ የሶሺያሊስት አመለካከት የነበራቸውን ክፍሎች ቢያስቆጣም፤ ኢህአፓ ምን ያህል ከራሱ የፖለቲካ እምነት ውጭም ወጥቶ ለህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ መብት የቆመ መሆኑን የሚመሰክር ጉዳይ ነበር። ምንም እንኳ ኢህአፓ እራሱ በጊዜው ይከተለው የነበረው የግራ ፍልስፍና ቢሆንም፤ በዚህ እምነቱ ላይ ብቻ ቆሞ የሌሎች ኢትዮጵያውያንን እምነትና ፍላጎት ሊጫን በፍፁም አለመፈለጉን ይመሰክራል። የዲሞክራሲ መብት ለሁሉም ይሰጥ ብሎ ከመሟገት በላይ ህዝባዊነት መመሳከሪያው ምን ሊሆን ይችላል? የኢህአፓ ትልቁ ሀይሉ፤ ህዝብን አስተምሮ በመለወጥ ያስተሳሰቡ ተጋሪ ለማድረግ የሚችል መሆኑን ከማመኑ ላይ ነው። በመሆኑም የመጡ መንግስታት በሙሉ ኢህአፓ ከህዝብ እንዳይገናኝ ይከላከላሉ። ህዝብን ተጭኖ የዲሞክራሲ መብቱን ነጥቆ በራሱ ቁጥጥር ስር በማዋል እኔ ብቻ ለስልጣን ልብቃ፤ እኔ ብቻ የሀገርን ችግር እፈታለሁ የሚል ቅዠት ውስጥ የገባ እንዳልነበር የሚመስከረው ይህ አይነቱ ጉዳይ ነው።

በዚህ ሁሉ ድርጊቱ ግን አንዳንድ ሰዎች ኢህአፓን ከደርግም ሆነ ከወያኔ ይብልጥ ሲኮንኑት ይስተዋላሉ። ለምን? ምክንያቶቹ ኢትዮጵያን ሊያጠፉ፤ የኢትዮጵያን ህዝብ ሊከፋፍሉ፤ ያቆተሙ ሀይሎችን በመደገፍ ወይም አራሳቸው በወንጀል ድርጊት ተጠያቂነትን በመፍራት። በመሆኑም ኢህአፓ በህዝብ ውስጥ ገብቶ እንዳይሰራ ይከላከላሉ። አላማቸው ሊሳካ የሚችለው ህዝብ በተወናበደ ሁኔታ ውስጥ ሲገኝ ብቻ በመሆኑ የማይሆን አሉባልታ ያናፈሳሉ። በጣም አሰቂኝ ከሆነው ድራማ ውስጥ ኢህአፓን ለማውቅ ዕድሜው የማይፈቅደለትን ህጻን በነሱ አካባቢ በመገኘቱ ብቻ በኢህአፓ ላይ እንዲህ ሲል እንዲናገር ይገፋፉታል "ወንድሜ የሞተው በኢህአፓ ነው" የሚለው ወጣት እንዴት ሆኖ ሲሉት፤ አባል ሆኖ ሞተ ይላል። ታዲያ! እንዲህ ያለው ወጣት የተወናበደ ለመሆኑ የወንድሙ ጉዳይ ሊሆን የሚችለው፤ የወንድሙንና የሀገሩን ዐላማ ተፃሮ በገዳይነት የተሰለፈው ሀይል ወይስ፤ እራሱ ወንድሙ የተዋደቀለት አላማ? ገዳዩ ማንኛው ነው? ይህን አይነቱ ወጣት ትክክለኛው የወንድሙ ገዳይ ማ! እንደሆነ በውል እንዳያውቅ ያወናብዱታል? የኢህአፓን መስመር ተከትለው የቆሙ ጀግኖች በራሳቸው እምነትና ቆራጥነት ለህዝባቸውና ለሀገራቸው ሲሉ መስዋዕትነት ከፈሉ እንጂ! እነዚያ የዩኒቨርስቲና የሁለተኛ ደረጃ ስመ ጥር ተማሪዎች አላዋቂ አልነበሩም። ባለማወቅም አልሞቱም። ኒስትሮው፤ተራ

ሰራተኛው፤ የቤት አገልጋዩ፤ገበሬው አምኖበት እንጂ! ላልገባው ዐላማ አልተሰዋም። እምነቱ ህዘባዊ መንግስት ነው። እምነቱ ዲሞክራሲ ያለገድብ ነው። ለዚህ እምነቱ ነወ የሞተው። ይህ ባለማወቅ የሚሞቱለት ጉዳይ የሚመስለን ካለን ተሳሰተናል። መስዋዕትነትን ፈርተን በየፈረንጁ ህገር ተጠግተን ባርነትን የምንለማመደው። እኛ ነን አላዋቂዎቹ። እኛ ነን ሀገርና ሰብአዊ ክብር በልምምጥ ይመጣል ብለን የምንጠብቅ። የጥንት አባቶቻችን ለሀገራቸውና ለህዝባቸው ቀናኢ በመሆን የጀግንነት መንፈስ በውስጣቸው ተቀርፆ ላደረጉት የህይወት መስዋዕትነት ተጠያቂው ኢትዮጵያዊነት እምነት ሊሆን አይችልም።

የዚህ አይነቱ ጭራና ቀንድ የሌለው ክስ በኢህአፓ ላይ ሲሰነዘር ሀገር ወዳጁና ሀቅ ፈላጊው ክፍል ዝም ብሎ መመልከት አይገባውም። ኢህአፓን በተለይ በአሁኑ ጊዜ ሊወነጅሉ የሚፈልጉ ሰዎች አላማቸው ምን እንደሆነ ለመረዳት አስቸጋሪ አይሆንም። በማይሆን ነገር ላይ ተነስቶ የገዳይን ምግባር ለተገዳይ ማሸከም አንድም ክጭፍን ጥላቻ አለያም ከፈሪ አገላጋይነት ስሜት የሚመነጭ ነው። ከዚህ አልፎም የጠላቶች ፕሮፓጋንዳ ሰለባ ከመሆን የዘለለ አይደለም። ምክንያቱም ቀጣይ ትግልን ለማኮሰመን የሚፈልጉ ናቸውና። በሀገሪቱ ህልውና ላይ ለመነገድ ያሰሉ ናቸውና። ወያኔን በመለማመጥ እራስን ማስጠጋት ይቻላል የሚሉ ናቸውና። አንዳንዶቹም ጊዜው እንጂ! ወንጀለኛነቱ ያለፈበት አይደለምና ኢህፓን በፍርሃት ቢጠሉት አያስገርምም። ይህ ሁሉ ትግል እንዳይካሄድ የሚያደርጉት ሙከራ ከመሆን አያልፍም።

ኢህአፓ፤ በዚያ ጊዜ በነበሩት ባለስልጣናት ላይ ቂም በቀል ቢኖረው ኖሮ! በተለያዩ ወቅቶች በሀገር ጉዳይ ላይ አብሮ ለመስራት እራሱን ባላቀረበ ነበር። ቂም በቀል ለህዝባዊው ዘላቂ ህይወት መፍትሄ ነው ብሎ ኢህአፓ አለማመኑን ይመሰክራል። አላማው የህዝብ መብትና የሀገር አንድነት ነውና። ኢህአፓ! ደጋግሞ ሲቃወም የሚስተዋለው ህዝብን ሲያሳፍኑ የነበሩ፤ ሲገድሉ ሲያሰቃዩ የነበሩ፤ ሀገርን ከማትወጣው መከራ ላይ የዳረጉ ግለሰቦች፤ አሁን ደግሞ የትግሉ አቀንቃኝ ሆነን እንታይ ሲሉ ነው። ይህ ደግሞ ለኢህአፓ ብቻ ሳይሆን ለማንኛውም ሀገር ወዳድ የሚዋጥ አይሆንም። ኢህአፓ በቆራጥ ህዝባዊነቱ በኢትዮጵያውያን ዘንድ የሚከበርበት እንጂ! የሚወነጀልበት ሊሆን አይችልም።

ኢህአፓ የአስመሳዮችን ደረባ፤ የህዝብ ጠላቶችን ጭፈራ፤ የምንተፉ ግብር ጣዮችን ድንኳን፤ ማፈራረሱ አይቀሬ የሆነባቸው ሁሉ ቢረባረቡ አያስደንቅም ። ሀገሬን ህዝቤን የሚል፤ ከጠላት ፕሮፓጋንዳ የተላቀቀ፤ ለዲሞክራሲያዊ መብት፤ ለባህል፤ ለቋንቋ ዕኩልነት፤ በአጠቃላይ ለህዝብ በጎነት፤ ለሀገር ነፃነት የቆመ ሁሉ ቢተባበር፤ በጥራትና በቆራጥነት የተደራጀ ሁሉ ቢወዳጅ፤ ኢህአፓ ደስታው እንደሚሆን ጥርጥር የለውም። በተረፈ ወያኔን መታገል የፈሩ፤ ከወያኔ በመለጠፍ የትግል መንገድን ያበላሹ፤ አሁንም ለማበላሸት የተሰለፉ፤ በወያኔ ያኮረፉ፤ በመለስ የተገፉ፤ በካድሬ የተገረፉ፤ ለንዋይ ያሰፈሰፉ፤ ዳግመኛ ምን ቢያሞድሙዱ ወያኔ በወዳጅነት የማይጥፍላቸው ሁሉ፤ በኢህአፓ ላይ የወሬ ዘመቻ ቢያካሄዱ፤ በራስ ጠብ ገላጋይ ሆኖ ከመታየት በላይ ፋይዳ አይኖራቸውም።

********************************************************************